# ደንብ

## የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS)

ተዛማጅ ሠነዶች፦ ACD, JEE, FAA
ሃላፊነት ያለው ፅ/ቤት፦ ዋና የሥራ ኃላፊ
የአካደሚ ዋና ኃላፊ Chief Academic Officer

## የተማሪ መዛወር እና አስተዳደራዊ ምደባዎች

I. **ዓላማ**

በካውንቲው ውስጥ ተማሪ ማዘዋወር እና አስተዳደራዊ ምደባዎችን በተመለከተ የአሰራር ሂደቶችን ለማዘጋጀት

II. **የበፊት መነሻ/አመጣጥ**

ተማሪዎች በመኖሪያ አካባቢ በተመሰረተዉ የመማሪያ ክልል ትምህርት ቤት ወይም በግላዊ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) በተመደቡበት ትምህርት ቤት መከታተል ይጠበቅባቸዋል። ከተማሪው(ዋ) የትምህርት ቤት ክልል ውጭ ወደሌላ ት/ቤት ለመከታተል የሚቀርብ ጥያቄ ከወላጅ/አሳዳጊ፣ ብቁ የሆነ (ች) ተማሪ (18 ዓመት ዕድሜ ላይ የደረሰ(ች) ወይም ከ18 ዓመት ዕድሜ በፊት የተፈቀደለ(ላ)ት)፣ ወይም በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሠራተኛ ሊቀርብ ይችላል።

III. **ትርጉም**

A. የአካባቢ ትምህርት ቤት ማለት የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ የጂኦግራፊያዊ ወሰን ድንጋጌን ተከትሎ ተማሪው(ዋ) የሚመደብበት/የምትመደብበት ትምህርት ቤት ነው። ተማሪው(ዋ) በትምህርት ቤት ምደባ የመቀየር ሂደት (COSA) አማካይነት ተዛዉሮ/ራ (እንደገና ተመድቦ/ባ) ከሆነ በማንኛውም ጊዜ ወደ የአካባቢ ትምህርት ቤት ለመመለስ ሊመርጥ/ልትመርጥ ይችላል/ትችላለች።

B. የተመደበ ትምህርት ቤት ማለት ተማሪው(ዋ) ለተወሰነ የትምህርት ዓመት የተመደበ(ች)በት ትምህርት ቤት ነው። ይህ የተፈቀደ COSA ከሌለ፣ በካውንቲ አቀፍ ማግኔት ወይም በሌላ ፕሮግራም መሣተፍ ከሌለ፣ ወይም አስተዳደራዊ ምደባ ካልሆነ የአካባቢ ትምህርት ቤት ነው። አንድ ተማሪ (COSA) ሲያገኝ/ስታገኝ፣ የተጠየቀው ትምህርት ቤት የተመደበበት ትምህርት ቤት ይሆናል።

IV. **የትምህርት ቤት ምደባ ለውጥ እንዲደረግ (COSA) ጥያቄ የሚቀርብበት የጊዜ ሰሌዳ እና የማመልከቻ ሂደቶች**

A. የማመልከቻ ሂደቶች

1. ወላጆች/አሳዳጊዎች/ ብቁ የሆኑ ተማሪዎች ከአካባቢያቸው ትምህርት ቤት ወደ ሌላ ት/ቤት ለመዛወር የMCPS Form335-45፣ የትምህርት ቤት ዝውውር ጥያቄ (COSA) በመጠቀም በሚከተሉት ምክንያቶች ጥያቄ ያቀርባሉ፦

   a) በማስረጃ የተረጋገጠ ልዩ ችግር/መከራ/እንግልት (Section V.A.) ይመልከቱ፣ ወይም

b) በሞንትጎመሪ ካውንቲ ውስጥ ቤተሰብ በቅርቡ የቦታ ለውጥ ሲያደርግ (Section V.B) ይመልከቱ፣ ወይም

c) በአንዳንድ ሁኔታዎች፣ታናሽ ወንድም/እህት በዕድሜ ትልቅ ከሆነ/ች ወንድም/እህት ጋር በተመሳሳይ ትምህርት ቤት እንዲሳተፍ/እንድትሳተፍ ስለመፍቀድ (Section V.C.) ይመልከቱ:-

2. MCPS ቅጽ 335-45፣ የ COSA ጥያቄ ፣ በእያንዳንዱ የ MCPS ት/ቤት እና በ MCPS ድረ-ገጽ ላይ ይገኛል፣ እና በበርካታ ቋንቋዎች ይገኛል።

3. የ COSA ጥያቄ፣ በካውንቲ አቀፍ ፕሮግራሞች፣ በክልል ፕሮግራሞች፣ ወይም ወደ እነዚህ ፕሮግራሞች መደረግ ያለበትን ፍትሓዊ ተደራሽነት ለማሳደግ በየዓመቱ ታትሞ በሚወጣና በሰፊዉ በሚሰራጭ ህትመት ላይ በት/ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ በግልጽ ለተለዩ ፕሮግራሞች የ MCPS ቅጽ 335-45፣ የ COSA ጥያቄ አስፈላጊ አይደለም።

B. የጊዜ ሰሌዳዎች

1. ለቀጣዩ ዓመት የ COSA ጥያቄዎች ተቀባይነት የሚኖራቸው በፌብሯሪ የመጀመሪያ የትምህርት ቀን እና በኤፐሪል ወር የመጀመሪያ የትምህርት ቀን መካከል ውስጥ ብቻ ነው።

2. ኤፐሪል ከመጀመሪያው የትምህርት ቀን በኋላ የሚቀርብ COSA ጥያቄ ተማሪው(ዋ) በሞንትጎመሪ ካውንቲ በአዲስ ነዋሪነት የመጣ(ች) ካልሆነ፣ ወይም ከኤፐሪል የመጀመሪያው የትምህርት ቀን አስቀድሞ ሊታሰብ የማይቻል አሳማኝ የሆነ ድንገተኛ ሁኔታ አጋጥሞ ካልሆነ በስተቀር ተቀባይነት አይኖረውም። ይህንን ሁኔታ የሚደግፍ ማስረጃ ማቅረብ ያስፈልጋል። የ COSA ጥያቄ በሂደት/በመጠባበቅ ላይ እያሉ ተማሪዎች በአባቢያቸው ትምህርት ቤት መመዝገብና መከታተል አለባቸው።

3. በኤፐሪል ወር በመጀመሪያው የትምህርት ቀን ወይም በፊት የቀረቡትን የ COSA ጥያቄን አስመልክቶ ውሳኔው እስከ ሜይ 31 ድረስ ለወላጆች/ሞግዚቶች/ብቃት ላላቸው ተማሪዎች ለማሳወቅ የተቻለ ጥረት ይደረጋል።

4. ተሞልቶ የተጠናቀቀው "MCPS Form 335-45" ቅጽ ከተሰጠው የጊዜ ገደብ በፊት ለተማሪው(ዋ) የአካባቢ ትምህርት ቤት ርእሰመምህር/ተወካይ መቅረብ አለበት።

a) የተማሪው(ዋ) የአካባቢ ትምህርት ቤት ርእሰመምህር/ተወካይ የነዋሪነት እና የቀረበውን ጥያቄ ማረጋገጫ ለመስጠት በቅጹ ላይ ይፈርማል/ትፈርማለች። እንዲህ ዓይነቱ ፊርማ በጥያቄው ላይ ስምምነት ተደርሷል ወይም ተቀባይነት አላገኘም ማለት አይደለም።

b) የተማሪው/ዋ የአካባቢ ትምህርት ቤት የተጠናቀቀውን ቅፅ ለአፈጻጸም ወደ Division of Pupil Personnel and Attendance Services (DPPAS) ያስተላልፋል።

c) DPPAS ውሳኔ ላይ ከመድረሱ በፊት ግምገማ ያጠናቅቃል።

5. በሁሉም ትምህርት ቤቶች የሚገኙ ልዩ ትምህርት የሚሰጣቸው ተማሪዎች (ለምሣሌ:- ንግግር እና ቋንቋ፣ የቤት ት/ቤት ሞዴል፣ የሠዓት ሥራ ሠራተኞች፣ ወይም የመማር እና የአካደሚክ ስንክልና አገልግሎቶች) መደበኛውን የ COSA ሂደት መከተል ይኖርባቸዋል። የተማሪው(ዋ) ግላዊ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) በሁሉ ትምህርት ቤቶች የማይሰጥ አይነት ልዩ ትምህርት

የሚጠይቅ ከሆነ፣ COSA ያስፈለገበትን ምክንያት የሚገልጹ ተገቢ ሠነዶችን ከማቅረብ በተጨማሪ ተማሪው(ዋ) በልዩ ፕሮግራም የተቀናበረ ልዩ ትምህርት እያገኘ(ች) መሆኑን ወላጅ/ሞግዚት በCOSA ጥያቄ ማቅረቢያ ቅጽ ላይ መግለጽ/መጠቆም አለባቸው። በሁሉም ት/ቤቶች የማይገኙ ልዩ የትምህርት ኣገልግሎቶች በመቀበል ላይ ለሚገኙ ተማሪዎች የሚደረጉ ጥያቄዎችን የሚመለከቱ ውሳኔዎች ከ ጁላይ 1 በኋላ ይደረጋሉ።

6. የ COSA ማመልከቻ ከታየ በኋላ ተቀባይነት ሊያገኝም ወይም ላያገኝም ይችላል፡-

    a) ጥያቄው የቀረበበት ምክንያቶች፤

    b) የልዩ ትምህርት አገልግሎት ለሚያገኙ ተማሪዎች IEP በተጠየቀው ትምህርት ቤት መተግበር ይቻል ይሆናል፤

    c) በተጠየቀው ትምህርት ቤት ውስጥ የሚመለከታቸው ሰራተኞችና አገልግሎቶች የሚገኙ ከሆነ፣

    d) የትምህርት ቤት አቅም እና ሌሎች ጉዳዮች አዳዲስ ተማሪዎችን ለመቀበል የሚያስችላቸው ከሆነ።

7. ለ COSA የቀረቡት ምክንያቶች ከተመረመረ በኋላ፣ እና የልዩ ትምህርት አገልግሎቶች ለሚቀበሉ ተማሪዎች በተጠየቀው ትምህርት ቤት የሚገኙትን የሰው ኃይል እና አገልግሎቶችን ግምት ውስጥ በማስገባት፣ IEP ሊተገበር ይችል እንደሆነ ታይቶ ፣ COSA ተቀባይነት ሊኖረው ወይም ተቀባይነት ላይኖረው ይችላል።

8. ወላጅ/አሳዳጊ/ብቁ ተማሪ ከ DPPAS የ COSA ጥያቄ መጽደቁን ወይም ውድቅ ለመደረጉ የጽሑፍ ማሳወቂያ ይደርሳቸዋል።

9. የቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት ማግኘቱን ወይም ውድቅ መደረጉን ለአካባቢ ት/ቤት እና ለተጠየቀበት ት/ቤት ይገለጽላቸዋል።

## V. COSA መጽደቅ የሚያስፈልገው የተማሪ ዝውውር መመሪያ/GUIDELINES FOR STUDENT TRANSFERS THAT REQUIRE AN APPROVED COSA

### A. ልዩ ችግር

1. ዝውውር፣ ወይም (COSAs)፣ የአንድ ቤተሰብ የግል ሁኔታ በትምህርት ቤት ለውጥ ምክንያት ሊቀየሩ የሚችሉ ልዩ ችግሮች ሲፈጠሩ ሊጠየቁ ይችላል። ይሁን እንጂ፣ ለብዙ ቤተሰቦች ችግር የሚሆኑ እንደ ዴይኬር ጉዳዮች ወይም የፕሮግራም/የኮርስ ምርጫ የመሳሰሉት፣ ሌሎች አስገዳጅ ምክንያቶች ከሌሉ በስተቀር የተለየ ከባድ ችግር ተደርጎ አይወሰድም።

2. ሁሉም የከባድ ችግር ጥያቄዎች ለየብቻ ሊረጋገጥ የሚችል ሰነድ ኣባሪ እንዲኖራቸው ያስፈልጋል፣ ኣለዚያ ጥያቄው ውድቅ ይደረጋል።

3. በተለየ ችግር ሁኔታ ምክንያት COSA ጸድቆላቸው አንደኛ ደረጃ ት/ቤት የሚማሩ ተማሪዎች ከአካባቢ ትምህርት ቤታቸው ወደ ሌላ የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ለመከታተል የሚጠይቁ ከሆነ ሌላ/አዲስ COSA ማመልከቻ ማቅረብ አለባቸው።

### B. የቤተሰብ ከነበሩበት ቦታ መቀየር/መንቀሳቀስ

ቤተሰባቸው ሞንትጎመሪ ካውንቲ ዉስጥ የቦታ ዝዉዉር/ቅያሪ ያደረጉ ተማሪዎች የነበሩበት ት/ቤት ለመቀጠል ከፈለጉ ምንም የከባድ ችግር ምክንያት ሳያቀርቡ COSA ለመጠየቅ ይችላሉ። እንዲህ ዓይነቱ ጥያቄ ተቀባይነት የሚኖረው ለቀሪው የትምህርት አመት ብቻ ሲሆን፣ በ11ኛ ወይም 12ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች ብቻ እስከሚመረቁ ድረስ ለመቆየት COSA ይፈቀድላቸዋል።

C. እህት/ወንድም

1. ታናሽ ወንድም/እህት ለመመዝገብ በፈለጉበት ዓመት፣ ታላቅ ወንድም/እህት መደበኛውን አጠቃላይ ትምህርት ወይም ልዩ ትምህርት ፕሮግራም በሚማርበት/በምትማርበት ትምህርት ቤት ታናሽ ወንድም/እህት COSA ለማመልከት ይችላል/ትችላለች። ለዚህ መመሪያ ዓላማ ወንድም/እህት የእንጀራ ወንድምንና እህትን እንዲሁም በእናት ወይም በአባት በኩል ወንድምን እና እህትን ያካትታል።

2. ታላቅ ወንድም/እህት ማግኔት፣ የቋንቋ ኢመርሽን፣ ወይም ሌላ የመተግበርያ ፕሮግራም ሲ(ስት)ከታተል፣ አንድ-በ-አንድ እታየ ለታናሽ ወንድሞች/እህቶች ለመደበኛ የት/ቤት ፕሮግራም COSA ሊፈቀድ ይችላል። የዚህ አይነት ፈቃድ በመማርያ ክፍል ቦታ የመኖር፣ የክፍል-ደረጃ ምዝገባ፣ የሰራተኛ ኣመዳደብ፣ ወይም በሚመለከታቸው ት/ቤቶች ላይ ተፅእኖ የሚያሳድሩ ሌሎች ታሳቢዎች ግንዛቤ ዉስጥ መግባት ኣለባቸው።

3. የክልል ለውጥ ከተከሰተ ከላይ የተዘረዘሩት ሰክሽን 1 እና 2 አይተገበሩም።

4. ለቋንቋ ኢመርዥን ፕሮግራሞች የወንድም/እህት ምርጫ የዕጣ መስፈርት በቦርድ ፖሊሲ JEE፣ Student Transfers ውስጥ ተገልጿል።

## VI. /ወዲያውኑ ሊጸድቅ የሚያስችል የተማሪ ዝውውር/ STUDENT TRANSFERS SUBJECT TO AUTOMATIC APPROVAL

የሚከተሉት የተማሪ ዝውውሮች ወዲያውኑ ሊፀድቁ ይችላሉ ሆኖም ግን MCPS Form 335-45 ማቅረብ ያስፈልጋል ለ COSA ጥያቄ በፋይል መዝግቦ ለማስቀመጥ

A. የተጣመሩ ት/ቤቶች ለ COSA ዓላማ እንደ አንድ ትምህርት ቤት ይቆጠራሉ፤ ይሁን እንጂ፣ ተማሪዎች በተጣመሩ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ፈቃድ ባለው COSA ውስጥ የሚማሩ ከሆነ፣ ተማሪዎች ከፍተኛዉን የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክፍል ለመማር ወዲያዉኑ የሚጸድቅ አዲስ የ MCPS Form 335-45፣ ለ COSA ጥያቄ ማቅረብ አለባቸው። እያንዳንዱ ማጣመር የዝውውር ትግበራ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳርፉ የሚችሉ ልዩ ባህሪያት አሉት።

B. በሞኖከሲ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Monocacy Elementary School) ለመከታተል ለሚፈልጉ በፑልስቪል አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Poolesville Elementary School) የተመደቡ ተማሪዎች MCPS Form 335-45፣ ለ COSA ጥያቄ ማቅረብ አለባቸው፣ ይህም ወዲያውኑ ተቀባይነት ይኖረዋል።

C. ምንም እንኳ አዲስ MCPS Form 335-45 ቅጽ ማቅረብ አስፈላጊ ቢሆንም፣ የ COSA ጥያቄ COSA በፀደቀላቸው የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች፣ ወይም በመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት የኤመርዥን ፕሮግራም በመሣተፍ ላይ የሚገኙ ተማሪዎች በፕሮግራሙ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ለመቀጠል ቢፈልጉ፣

መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት እንዳለው የመጋቢነት ቅጥ አይነት(feeder pattern) ወዲያውኑ ሊፀድቅላቸው ይችላል። አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተማሪዎች በኮንሰርሽያ ሂደት ሊመደቡ ይችላሉ። ጥያቄው በክፍል "Section IV" ባሉት የጊዜ ገደቦች እና የማመልከቻ ሂደቶች መሰረት መቅረብ አለበት። በ Section VII.A. ያለው አትሌቲክስ ለመሣተፍ አለመቻል ሊሠረዝ ይችላል። በዳወንካውንቲ ኮንሰርሽየም መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ልዩ ፕሮግራሞች የሚገኙ ከክልል ውጭ የሆኑ ተማሪዎች ለዳወንካውንቲ ኮንሰርሽየም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዕጣ ለመሣተፍ ዋስትና አላቸው።

## VII. አጠቃላይ ድንጋጌዎች

### A. አትሌቲክስ

ከራሳቸዉ መጋቢ ት/ቤት ዉጪ COSA የሚያገኙ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች በአትሌቲክስ ውስጥ ከመሳተፋቸው በፊት በአዲሱ ትምህርት ቤት ለአንድ ዓመት መማር አለባቸው። ሆኖም ግን፣ ስለ COSA ምክንያት በመግለጽ ለሲተም አቀፍ የአትሌቲክስ ዳይረክተር እንዲሠረዝ በጽሑፍ መጠየቅ ይቻላል። ሥረዛዎች በተለዩ ሁኔታዎች/ምክንያቶች ሊሰጡ ይችላሉ።

### B. መጓጓዣ/ትራንስፖርት

የፀደቀላቸውን COSA የሚቀበሉ ተማሪዎች ወላጆች/ሞግዚቶች/ብቁ ተማሪዎች ስለመጓጓዣ ሃላፊነት ይወስዳሉ።

### C. ወደ አካባቢ ትምህርት ቤት መመለስ

1. አንድ ተማሪ በ COSA ሂደት አማካይነት እንደገና ከተመደበ/ች፣ ተማሪው(ዋ) በማንኛውም ጊዜ ወደ አባቢ ት/ቤት መመለስን መምረጥ ይችላል/ትችላለች። ይህ ደንብ ለአስተዳደራዊ ምደባዎች አይተገበርም። (ክፍል/Section VIII ይመልከቱ)

2. ልዩ ሁኔታዎች ሲከሰቱ፣ COSA ለአንድ አመት ብቻ ሊፈቀድ ይችላል። በተጨማሪ፣ አንድ ቤተሰብ በትምህርት አመት ውስጥ በሚንቀሳቀሱበት ሁኔታዎች ውስጥ፣ COSA የትምህርት ዓመቱ እንዲጠናቀቅ ብቻ ሊሰጥ ይችል ይሆናል (በተጨማሪ ከላይ ያለውን ክፍል V.B. ይመልከቱ)። በዚህ ሁኔታ ውስጥ፣ ወላጆች/ሞግዚቶች/ብቃት ያላቸው ተማሪዎች በቀጣዩ የትምህርት ዓመት COSA በተመደቡበት ትምህርት ቤት ለመቀጠል እንደገና ካላመለከቱና ካልተቀበሉ ተማሪዎች ወደ አካባቢያቸው ትምህርት ቤት መመለስ አለባቸው።

3. ርእሰመምህር በተገቢ ምክንያት የተማሪው/ዋ COSA እንዲሰረዝ መጠየቅ ይችላል/ትችላለች - ለምሳሌ፣ ቀጣይ የስነስርዓት ጥሰት ወይም የትምህርት ክትትል ችግሮች ካሉ።

4. በካውንቲ አቀፍ ወይም በክልላዊ ፕሮግራሞች ውስጥ በመሳተፋቸው ምክንያት ከትምህርት ቤታቸው ሌላ ትምህርት ቤት የሚማሩ ተማሪዎች በዚህ ፕሮግራም ውስጥ መሳተፍ ካቆሙ ወደ አካባቢ ትምህርት ቤታቸው እንዲመለሱ ይጠበቅባቸዋል።

5. ለረጅም ጊዜ ከትምህርት ቤት እገዳ በኋላ የ COSA ጥያቄዎች ከትምህርት ቤቱ ርእሰ መምህር ጋር በመመካከር በ DPPAS ይታያሉ። ለዚህ ምክንያት የትም/ቤት ለውጦች በአጠቃላይ ፈቃድ አይኖራቸውም።

D. በኮንሰርሽያ ውስጥ ትምህርት ቤት ምደባ መቀየር

በኮንሰርሽያ ክልል ውስጥ የሚኖሩ ተማሪዎች፣ በማስረጃ የተረጋገጡ ልዩ የሆነ ችግር ያለባቸው እና በኮንሰርሽየም ውስጥ ሌላ ትምህርት ቤት ለመማር የሚፈልጉ ከሆነ፣ COSA ቅጽ ማስገባት አይኖርባቸውም፣ ግን የይግባኝ ደብዳቤ ለ Consortia Choice and Application Program አገልግሎቶች ማቅረብ ያስፈልጋል።

## VIII. በአስተዳደር የሚደረጉ ምደባዎች

A. በርእሰመምህር ተነሳሽነት የሚደረግ አስተዳደራዊ ምደባ

1. ለአስተዳደራዊ ምደባ ጥያቄ ከመቅረቡ በፊት፣ ለተማሪው(ዋ) ትምህርት ቤት የተመደበ ርዕሰመምህር/ት እና የተማሪ ፐርሶኔል ሰራተኛ-

   a) የተማሪን የትምህርት፣ የህክምና፣ እና የባህርይ መዝገቦችን መገምገም እና የተለያዩ የትምህርት ቤት ምደባዎችን ማገናዘብ፣ እና

   b) ከወላጅ/ሞግዚት እና ተማሪ ጋር የስብሰባ ከፍለጊዜ/ቀጥሮ መያዝ።

2. የአስተዳደር ምደባ ሁኔታ ከተገለፀ፣ የሚከተሉት እርምጃዎች ተግባራዊ ይሆናሉ፡-

   ሀ) በአስተዳደራዊ የምደባ ሂደት ምክንያት፣ ከርእሰመምህር እና በትምህርት ቤት ድጋፍ እና ማሻሻያ ጽ/ቤት (OSSI) አግባብነት ካለው የአካባቢ ተባባሪ ሱፐርኢንተንደንት ጋር በመማከር የ DPPAS ዳይሬክተር ለተማሪው(ዋ) አመቺ የሚሆን የት/ቤት ምደባ ቦታ ያረጋግጣል/ታረጋግጣለች።

   b) የፐዩፐል ፐርሶኔል ሰራተኛ ከወላጅ/ሞግዚት፣ ተማሪ፣ የተቀባዩ ትምህርት ቤት ርስእሰመምህር እና የተማሪ እና የቤተሰብ ድጋፍ እና ተሳትፎ ጽ/ቤት (OSFSE) ሰራተኞች ጋር ማንኛዉንም አስፈላጊ ኮንፍረንሶች ማዘጋጀት፣ እንዲሁም ስለምደባ፣ ስለ አትሌቲክስ ብቁነት እና የአትሌትክስ የሚሠረዝበትን ሂደት የጽሁፍ ማረጋገጫ ያቀርባል/ታቀርባለች።

B. በ OSFSE አነሳሽነት የሚካሄድ አስተዳደራዊ ምደባ

ልዩ ሁኔታዎች ሲከሰቱ ከወላጅ/ሞግዚት/ብቁ የሆነ ተማሪ፣ ከአካባቢው የት/ቤት ሠራተኞች ጋር፣ በተጨማሪም ከሚመለከተው የአካባቢው ተባባሪ የ OSSI ሱፐርኢንተንደንት ጋር በመነጋገር በማናቸውም ጊዜ አስተዳደራዊ ምደባው በ OSFSE ተባባሪ ሱፐርኢንተንደንት ወይም በተወካይdesignee አማካይነት ሊከናወን ይችላል። የ DPPAS ዲሬክተር በ OSFSE አነሳሽነት የተደረጉ አስተዳደራዊ ምደባዎችን ያጸድቃል/ታጸድቃለች ወይም ውድቅ ያደርጋል/ታደርጋለች።

C. የ OSFSE ሰራተኞች አስተዳደራዊ ምደባ የተደረገላቸውን ተማሪዎች የአካደሚያዊ እርምጃ እና ማህበራዊ ተግባቦትን የመቆጣጠር ኃላፊነት አለባቸው።

D. በዚህ ድንጋጌ መሠረት፡- በሥነምግባራቸው በትምህርት ቤት ክልል ለሌሎች ጤንነት እና/ወይም ደህንነት ስጋት በመፍጠራቸው ምክንያት የተዛወሩ ተማሪዎች በአትሌቲክስ ለመሣተፍ ብቁ ለመሆን በተዛወሩበት ት/ቤት አንድ የትምህርት አመት መከታተል ይኖርባቸዋል። እንዲሠረዝ የ COSA ምክንያቶችን በማብራራት ለስርአት አቀፍ አትሌቲክስ ዲሬክተር ወላጆች ሊያመለክቱ ይችላሉ።

IX. ይግባኝ

A. የትምህርት ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ

1. አንድ COSA በ DPPAS ዳይሬክተር ከተከለከለ፣ ወላጅ/አሳዳጊ/ብቁ ተማሪ ውሳኔውን ለትምህርት ቤቶች የበላይ ዋና ተቆጣጣሪ/ተወካይ ይግባኝ ማቅረብ ይችላሉ።

2. የተከለከለበት ይግባኝ ጥያቄ እየተካሄደ እያለ ተማሪው(ዋ) በአካባቢ ትምህርት ቤት ተመዝግቦ(ባ) መከታተል አለበ(ባ)ት።

3. ይግባኝ በፅሑፍ መቅረብ ያለበት ሲሆን ለዋና የሥራ ኃላፊ ጽ/ቤት የውሳኔ ደብዳቤ ላይ ከተጠቀሰው ቀን ጀምሮ ባሉት 15 ቀናት ውስጥ መድረስ አለበት (ዋና የሥራ ኃላፊ እንደ ት/ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ ተወካይ ሆኖ ያገለግላል/ሆና ታገለግላለች)።

4. ይግባኙ ላይ ውሳኔው እንደገና እንዲታይ ያስፈለገበትን ምክንያት መገለጽ አለበት። ይግባኝ ለማቅረብ ተብሎ ተጨማሪ መረጃ መስጠት አያስፈልግም፣ ሆኖም ግን ይግባኝ አቅራቢ ለማንኛውም ከግምት ውስጥ መግባት ያለበትን ተጨማሪ ማስረጃ ማካተት አለበት/ባት።

   የትምህርት ቤቶች ዋና ተቆጣጣሪ፣ ወይም ዋና የሥራ ኃላፊ እንደ ዋና ተቆጣጣሪ ተወካይ በመሆን ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት ያሉትን ሁሉንም ማስረጃዎች ይገመግማሉ።

5. ምንም እንኳን ጉዳዩች የሚገናዘቡት በቀረቡት ሠነዶች እና በስልክ ስብሰባዎች ላይ ተመስርቶ ቢሆንም፣ በዋና የሥራ ኃላፊ hearing officer አማካይነት በአካል ተሰብስቦ ኃሳብን የመግለጽ እድል ማዘጋጀት ይቻላል።

6. ቁጥሩን፣ ውስብስብነቱን እና በአንድ ጊዜ/በተመሣሣይ ጊዜ የሚስተናገደውን ይግባኝ ጊዜ ግምት በመስጠት ውሳኔዎች በፍጥነት ይከናወናሉ።

7. ከጁላይ 1 በፊት ለዋና የሥራ ኃላፊ የቀረቡ ይግባኞች ትምህርት ቤት ከመጀመሩ በፊት ይወሰናሉ።

ለ. የትምህርት ቦርድ

1. በት/ቤቶች ዋና የበላይ ተቆጣጣሪ/ተወካይ የተደረገ ውሳኔ ይግባኝ በሱፐርኢንተንደንቱ የውሳኔ ደብዳቤ ላይ ከተጠቀሰው ቀን አንስቶ በ30 የካላንደር ቀናት ውስት ለትምህርት ቦርድ መድረስ አለበት።

2. አቤቱታ አቅራቢዎች የሚያቀርቡትን ይግባኝ በተቻለ ፍጥነት እንዲያደርጉት ይበረታታሉ።

3. ቦርዱ ይግባኙን ከመመርመሩ በፊት፣ ለትምህርት ቤቶች ዋና የበላይ ተቆጣጣሪ/ተወካይ ቅጂውን/ኮፒ ለይግባኝ ጠያቂው/ዋ ተደርጎ ምላሽ እንዲሰጥ/ድትሰጥ እድል ይሰጠዋል/ጣታል።

4. የቦርድ ውሳኔ በቦርድ ፖሊሲ/Board Policy BLB ላይ ያለውን ሥርዓት በመከተል በጽሑፍ ይሰጣል፣ የአቤቱታ እና የይግባኝ ደንቦች ።

**ስለ መመሪያው/ደንቡ ታሪክ፡-** የቀድሞው የፌብሯሪ 22/1980 መመሪያ/ደንብ/Regulation 265-2፣ ጃኑዋሪ 23/1992 ክለሣ ተደርጓል፣ ኤፕሪል25/1994 ተሻሽሏል፣ ዲሴምበር 23/1994 ማሻሻያ ተደርጎበታል፣ ዲሴምበር 30/1997 ተሻሽሏል፣ ጁላይ20/1998 ማሻሻያ ተደርጓል፣ ዲሴምበር 2/1999 ተሻሽሏል፣ ጁን 1/2000 የጽ/ቤቱ

ስያሜዎች ተሻሽለዋል/updated office titles፣ ዲሴምበር6/2000 ማሻሻያ ተደርጓል፣ ጃኑዋሪ 7/2002 ተሻሽሏል፣ ጃኑዋሪ 10/2003 ክለሳ ተደርጓል፣ ኖቬምበር 29/2006 ማሻሻያ ተደርጓል፣ non-substantive revision፣ ኖቬምበር 27/2007፣ non-substantive revision፣ ኖቬምበር 17/2008፣ ጃኑዋሪ 04/2010 ክለሳ ተደርጓል፣ ኖቬምበር 18/2010 ማሻሻያ ተደርጓል፣ ዲሴምበር 12/2011 ተሻሽሏል፣ ዲሴምበር 20/2012 ተሻሽሏል፣ ኖቬምበር 6/2013 ክለሳ ተደርጎበታል፣ ዲሴምበር 13/2013ማሻሻያ ተደርጎበታል፣ ኤፕሪል 5/2018 ማሻሻያ ተደርጓል፣ ጃኑዋሪ 7/2019 ተሻሽሏል።